# ዜና አመዝኤ



የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ፤ ቅፅ 13 ቁጥር 3 ጥቅምት 1999

## ለሱማሌ ክልል የጎርፍ አደጋ ተጎጂዎች የአስቸኳይ ጊዜ ምግብና ቁሳቁስ ዕርዳታ በመቅረብ ላይ ይገኛል

### ከፍተኛ የፌደራልና የክልሉ መንግሥት ባለሥልጣናት በጎርፍ የተጎዱትን አካባቢዎች ጎበኙ

በሱማሌ ክልል ጎዴ ዞን በሚገኙ አምስት ወረዳዎች እንዲሁም በአፍዴር ዞን በሚገኝ አንድ ወረዳ የዋቢ ሸበሌ ወንዝ ሙላት ባስከተለው የጎርፍ መጥለቅለቅ ለተፈናቀሉ ከ150 ሺህ በላይ የሚሆኑ ሰዎች የአስቸኳይ ጊዜ ምግብና ቁሳቁስ ዕርዳታ እየቀረበ ነው::

በጎዴ ዞን ከሚገኙ ሰባት ወረዳዎች  አምስቱ ማለትም ቀላፎ ፣ ሙስታሒል ፣ ፊርፊር፣ ምስራቅ ኢሚ እና ምዕራብ ጎዴ ወረዳዎች ፣ እንዲሁም በአፍዴር ዞን የምዕራብ ኢሚ ወረዳ በውሀ መጥለቅለቅ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ ታውቋል::  በነዚህ ወረዳዎች የዋቢ



ሸበሌ ወንዝ ሙላት ባስከተለው መጥለቅለቅ ከ300 ሺህ በላይ የሚሆኑ ሰዎች በጎርፉ አደጋ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ ፣ ከ80 በላይ ወገኖቻችን በጎርፍ አደጋው ህይወታቸውን ማጣታቸው እንዲሁም እስከ 3 ሺህ የሚደርሱ እንስሳት እና በርካታ የቤት ንብረቶች ከመወሰዳቸውም በላይ የውሀ ጠምጠች ፣ በእርሻ ላይ ያለ ሰብል እና ግጦሽ መውደሙን መረጃዎች ያመለክታሉ::

በአደጋው ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉት ወገኖች መርጃ ፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ከመደበው 50 ኩንታል ሀይል ሰጪ ብስኩት ፣ 25 ኩንታል አልሚ ምግብ ፣ መጠናቸው 4 ሜትር በ50 ሜትር  የሆኑ 20 ጥቅል የመጠለያ ኘላስቲክ ሸቶች ፣ 180 ተጣጣፊ ጀሪካን ፣ 4 ሺህ ኩባያ ፣ 4 ሺህ ሳህን ውስጥ ከድሬዳዋ ማዕከላዊ መጋዘን 10 ኩንታል አልሚ ምግብ ፣ 20 ኩንታል /178 ካርቶን/ ብስኩት ፣ 10 ጥቅል ኘላስቲክ ሸቶች ፣ 100 ተጣጣፊ ጀሪካን ፣ 2 ሺህ ኘላስቲክ ኩባያ፣ 1 ሺህ ኘላስቲክ ሰሀንና 1008 ጥንድ አንሶላዎች ጥቅምት 23 ቀን 1999 ዓ.ም በአይሮኘላን ጎዴ ድረስ ከተጓጓዘ በኋላ ከመከላከያ በተገኘ ሄሊኮኘተር ለተረጂዎች እንዲደርስ መደረጉ ታውቋል::  ከዚህም በተጨማሪ ለተጎጂ ወገኖች ከተመደበው 19 ሺህ 721 ኩንታል የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ውስጥ 19 ሺህ ኩንታል የምግብ እህል፣ አልሚ ምግብ ፣ ጥራጥሬና ዘይት በጭነት ተሽከርካሪዎች ጉዳቱ

በዚህ ዕትም ውስጥ


በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ ከ ብር 35 ሚለዮን በላይ ተለግሷል::
*ገጽ 3*

በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች ከ 27 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ፣ ከ104 ሺህ በላይ የመገልገያ ቁሳቁስ ተልኳል::
*ገጽ 5*

ለጥቅምት ወር ከ 176 ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል::
*ገጽ 6*

የብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ የዕርዳታ አሰባሰብ መርሀ ግብር አፀደቀ ለጎርፍ ተጎጂ ወገኖች ሁሉም የበኩሉን ድጋፍ እንዲያበርክት ጥሪ አቀረበ
*ገጽ 7*

ከ29 ሚሊዮን በላይ ዕርዳታ ለማሰባሰብ መታቀዱ ተገለፀ
*ገጽ 8*

የስጠርት የሙዚቃ እና  የትያትር ዝግጅት ኮሚቴ የዕርዳታ ማሰባሰብ ኘሮግራሙን ይፋ አደረገ
*ገጽ 10*



በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 5529259
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣ www.dppc.gov.et

ወደደረሰባቸው አካባቢዎች መጓጓዙ እንዲሁም እንደችግሩ ስፋትና መጠን እየታየ ተጨማሪ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብና ቁሳቁስ ዕርዳታዎች በተከታታይ ወደ ስፍራው ለማጓጓዝ ዝግጅት መደረጉንም ለማረጋገጥ ተችሏል። በተያያዘም በውሃ ተከበው የሚገኙ ሰዎችን ለማውጣትና የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ እና ቁሳቁስ ዕርዳታዎችን ወደ አስቸጋሪ ቦታዎች በማቅረቡ ሥራ የሚያግዙ 10 ጀልባዎችና 22 አባላት ያሉበት ወታደራዊ የህይወት አድን ቡድን በቆላፎና ሙስታሔል ወረዳዎች የህይወት ማዳን እና የምግብና ቁሳቁስ ዕርዳታ የማቅረብ ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ። የጎርፍ አደጋ የሚገኝበትን ሁኔታ ፣ የምግብና ቁሳቁስ ዕርዳታ አቅርቦቱን ሒደት እና ተዛማጅ ጉዳዮችን በቅርበት በመከታተል እና በማጥናት ለቀጣይ ዕርምጃ የሚረዱ ሪፖርቶችን በየዕለቱ ከስፍራው የሚያስተላልፉ ሁለት የፌዴራል አመዝኤ ባለሙያዎችም ተመድበው በአካባቢው በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸው ታውቋል።



ለተጎጂ ወገኖች ከተመደበው 19 ሺህ 721 ኩንታል የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ውስጥ 19 ሺህ ኩንታል የምግብ እህል፣ አልሚ ምግብ ፣ ጥራጥሬና ዘይት በጭነት ተሽከርካሪዎች ጉዳቱ ወደደረሰባቸው አካባቢዎች መጓጓዙ እንዲሁም እንደችግሩ ስፋትና መጠን እየታየ ተጨማሪ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብና ቁሳቁስ ዕርዳታዎች በተከታታይ ወደ ስፍራው ለማጓጓዝ ዝግጅት መደረጉንም ለማረጋገጥ ተችሏል።



ይህ በእንዲህ እንዳለም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስትር አቶ አዲሱ ለገሠ የተመራውና የአመዝኤ ም/ዋና ዳይ ክተር ቡድን የክልሉ ርዕሰ መስተዳደር በተገኙበት ከጥቅምት 23 ቀን 1999 ጀምሮ ለ 2 ቀናት ሰሞኑን በጎርፍ መጥለቅለቅ የተጎዱትን አካባቢዎች ተዘዋውረው ጎብኝተዋል።

በዚሁ ጉብኝት ወቅት ም/ጠቅላይ ሚኒስትርና የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስትር አቶ አዲሱ ለገሠ አደጋው ባለፈው ክረምት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የደረሱት የጎርፍ አደጋዎች ካደረሱት ጉዳት ባላገገምንበት እና ባልታሰበ ወቅት የደረሰ እና ያስከተለውም ጉዳት በዓይናችን እንዳየነው ከፍተኛ እና አሳዛኝ ነው ካሉ በኋላ በውሀ ተከበው ለህይወታቸው አስጊ በሆነ ቦታ የሚገኙ ሰዎችን በአስቸኳይ የማውጣቱ እና በአደጋው ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉት የአስቸኳይ ጊዜ ምግብና ቁሳቁስ ዕርዳታ የማቅረቡ ሥራ ጎን ለጎን ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን አረጋግጠዋል። በማያያዝም አካባቢው የሚገኝበት ርቀት እና ያለበት የማጓጓዣ መሠረተ ልማት እጥረት ለተረጂዎች የሚያስፈልገውን ዕርዳታ በተፈለገው ፍጥነት ለማድረስ በሚደረገው ጥረት ላይ የራሱ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ቢሆንም በተገኘው የማጓጓዣ ዘዴ እና በተቻለ ፍጥነት ዕርዳታው እንዲደርሳቸው ለማድግ ጥረት ይደርጋል ብለዋል ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ አዲሱ ለገሠ።

የአደጋ መከላከልና ዝግጅነት ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገብረመድህን በላይ በበኩላቸው የሱማሌ ክልል በአገራችን ለድርቅ ተጋላጭ ከሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች አንዱና ዋነኛው እንደመሆኑ ባለፉት ዓመታት አመዝኤ በክልሉ በተከሰቱት ተከታታይ የድርቅ አደጋዎች ተጎጂ ለሆኑት ወገኖች አስፈላጊ የሆኑትን የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች ሲያቀርብ መቆየቱን

አመዝኤ

አስታውሰው አሁንም የጎርፉ አደጋ መከሰት ከተሰማበት ዕለት ጀምሮ አመዝኤ የጎርፍ ሰለባ ለሆኑት ወገኖች አስፈላጊውን የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ለማቅረብ



ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስትር አቶ አዲሱ ለገሠ የተመራውና የአመዝኤ ም/ዋና ዳይ ክተር ቡድን የክልሉ ርዕሰ መስተዳደር በተገኙበት ከጥቅምት 23 ቀን 1999 ጀምሮ ለ 2 ቀናት ሰሞኑን በጎርፍ መጥለቅለቅ የተጎዱትን አካባቢዎች ተዘዋውረው ጎብኝተዋል።

መንቀሳቀሱን ገልዋል። ምንም እንኳን አካባቢው ያለበት ርቀት እና የትራንስፖርት ችግር ለተጎጂዎች የሚጓጓዘው ዕርዳታ በሚፈለገው ፍጥነት እንዳይደርስ ሳንካ ቢሆንም በአየር ሊጓጓዝ የሚችለውን ዕርዳታ የማቅረቡ ሥራ መጀመሩንና በምድር የሚጓጓዘው ደግሞ ወደተረጂዎቹ ለማድረስ የተወሰኑ ቀናትን ሊወስድ እንደሚችል ጠቁመዋል። አያይዘውም አቶ ገ/መድህን በአየር ሊጓጓዙ የሚችሉ የአስቸኳይ ጊዜ ምግብና ቁሳቁስ ዕርዳታዎችን ከድሬዳዋ ጎዴ በአየር እንዲሁም ከጎዴ አደጋው ወደ ደረሰባቸው አካባቢዎች ከመከላከያ በተገኘ ሔሊኮፕተር የማድረሱ ሥራ የተጀመረ እና ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን፣ በምድር የሚጓጓዘውን ዕርዳታ በተመለከተም ከመከላከያ ሠራዊት እና ከሌሎች የሚመለከታቸው የክልሉና የፌዴራል አካላት ጋር በመነጋገር በተቻለ ፍጥነት በቶሎ የሚደርስበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ጥረት እንደሚደረግ ገልፀዋል። በመጨረሻም የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ አብዱላሂ ሐሰን የዋቢ ሸበሌ ሙላት ባስከተለው የውሀ መጥለቅለቅ በተለይ በአምስት ወረዳዎች በሰው እና በንብረት ላይ የጎርፍ አደጋ ያስከተለውን ጉዳት ተዘዋውረው የተመለከቱት የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው ፣ በተፈጥሮ አደጋ ሳቢያ ጉዳት በደረሰ ጊዜ ከክልሉም ሆነ ከፌዴራል መንግስት የሚጠበቀው በአደጋው የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችሉ ወቅታዊና ተገቢ እርምጃዎች መውሰድ ነው ብለዋል። በክልሉ መንግሥት በኩል የጎርፍ ተጎጂዎችን ለመታደግ የሚቻለው ሁሉ እንደሚደረግ ያረጋገጡት ርዕሰ ማስተዳድሩ የጎርፍ አደጋ ያስከተለውን ጉዳት ተዘዋውረው የተመለከቱት የፌዴራል መንግሥት ባለሥልጣናትንም ለችግሩ ለሰጡት ትኩረት ካመስገኑ በኋላ ለአደጋው ተመጣጣኝ የሆነ ምላሽ ለመስጠት ተገቢውን ድጋፍ እንደሚያደርጉ ያላቸውን እምነት ገልፀዋል።

## በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ ከ ብር 35 ሚለዮን በላይ ተለግሷል።

ባሳለፍነው ክረምት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የጣለው ከባድ ዝናብ ባስከተለው የጎርፍ እና የውሃ መጥለቅለቅ አደጋ ጥሪታቸውን ላጡና ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች መርጃ ከአገር ውስጥ የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሠራተኞቻቸው ፣ ማህበራት ፣ የሀይማኖት ተቋማት እና ግለሠቦች ፣ ከአገር ውጭ የውጭ መንግስታትና ድርጅቶች ፣ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የተለያዩ ግለሠቦች እስከ ጥቅምት 28 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ብር 46 ሚሊዮን 044 ሺህ 969 ከ64 ሣንቲም በጥሬ ገንዘብና በዓይነት

የለገሱ መሆኑ ታውቋል::

እስከተጠቀሰው ጊዜ ድረስ ከተለገሰው ጠቅላላ የዕርዳታ መጠን ውስጥ ብር 35 ሚሊዮን 238 ሺህ 213 ከ50 ሳንቲም በጥሬ ገንዘብ ቀሪው ብር 10 ሚሊዮን 806 ሺህ 756 ከ14 ሳንቲም ደግሞ በዓይነት የተለገሠ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል::

ባሉት ሶስት ወራት ውስጥ ቁጥራቸው ከ980 በላይ የሆኑ የመንግሥስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሠራተኞቻቸው ፣ የልማት ድርጅቶች ፣ ማህበራት ፣ የግል ድርጅቶች ፣ የሀይማኖት ተቋማት ፣ የክልል መንግስታት ፣ የመከላከያ ሠራዊት አካላት ፣ የፖሊስ አካላት እና ግለሠቦች ከብር 5 ጀምሮ እስከ ብር 1.4 ሚሊዮን የሚደርስ ዕርዳታ የለገሡ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::



ከተለገሰው ጠቅላላ የዕርዳታ መጠን ውስጥ ብር 35 ሚለዮን 238 ሺህ 213 ከ50 ሳንቲም በጥሬ ገንዘብ ቀሪው ብር 10 ሚሊዮን 806 ሺህ 756 ከ14 ሳንቲም ደግሞ በዓይነት የተለገሠ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል::



ሌላም በኩል በጥሬ ገንዘብ ከተለገሠው ብር 35 ሚለዮን 238 ሺህ 213 ከ50 ሳንቲም ውስጥ ብር 26 ሚሊዮን 638 ሺህ 213 ከ50 ሳንቲም በማዕከል የተሰበሰበ ሲሆን ቀሪው ብር 8 ሚሊዮን 600 ሺህ ደግሞ በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል የተሰበሰበና በዛው የሚገኝ መሆኑን እንዲሁም በዓይነት ከተለገሠው ብር 10 ሚሊዮን 806 ሺህ 756 ከ14 ሳንቲም ውስጥ ብር 6 ሚሊዮን 206 ሺህ 756 ከ14 ሳንቲም የሚገመተው በማዕከል ቀሪው ብር 4 ሚሊዮን 600 ሺህ የሚገመተው ደግሞ በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል የተለገሠ መሆኑን የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ::

በአጠቃላይ በጎርፍ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ የሀገር ውስጥ ዕርዳታ የማሰባሰቡ ሥራ ከተጀመረበት ነሐሴ 2 ቀን 1998 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 28 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ

በተመሳሳይም በጎርፍ ለተጎዱ ወገኖቻችን የገንዘብና የዓይነት ዕርዳታ ከለገሡት የውጭ መንግስታትና ድርጅቶች እንዲሁም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን መካከል የአፍሪካ ህብረት 100 ሺህ ዶላር ፣ የተባበሩት የታንዛንያ ሪፐብሊክ መንግስት 100 ሺህ ዶላር፣ የሞዛቢክ ኢምባሲ 1 ሺህ 200 ዶላር ፣ በባህ ን የኢትዮጵያውያን ኮሙኒቲ 7 ሺህ 851 ዶላር ፣ በቻይና የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን 5 ሺህ 650 ዶላር ፣ በቤይሩት የኢትዮጵያዊያን ኮሙኒቲ 130 ሺህ 196 ብር ከ19 ሳንቲም የለገሡ መሆኑ ይጠቀሳል::

በተያያዘም በዓይነት ዕርዳታ ከለገሡት የውጭ መንግስታት መካከል ጃጠን ፣ ሊቢያ፣ ግብጽ ፣ አልጀሪያ ፣ ማልታ እና የኦስትሪያ ቀይ መስቀል ተጠቃሽ ናቸው::

# በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች ከ 27 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ፣ ከ104 ሺህ በላይ የመገልገያ ቁሳቁስ ተልኳል።

ከሐምሌ እስከ መስከረም ባሉት ወራት ውስጥ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖቻችን መርጃ የሚውል ከ27 ሺህ 682 ኩንታል እህልና አልሚ ምግብ ፣ ከ104 ሺህ 55 ቁሳቁስና 404 ሺህ የጎርፍ መከላከያ ግድብ መስሪያ ጆንያ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አማካይነት ተልኮ መፋፈሉ ተገለፀ።

ብርድልብስ ፣ 1ሺህ 150 ፍራሽና 404ሺህ የጎርፍ መከላከያ ግድብ መስሪያ ጆንያ በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ለሁሉም ክልሎች መላኩ ታውቋል።

ይኸው ዕርዳታ እንደ ችግሩ ስፋትና ክብደት መጠን እየታየ የተላከ ሲሆን በዚሁ መሠረት ለአማራ ክልል የጎርፍ ተጎጂዎች 7ሺህ 219

ከሐምሌ እስከ መስከረም ባሉት ወራት ውስጥ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖቻችን መርጃ የሚውል ከ27 ሺህ 682 ኩንታል እህልና አልሚ ምግብ ፣ ከ104 ሺህ 55 ቁሳቁስና 404 ሺህ የጎርፍ መከላከያ ግድብ መስሪያ ጆንያ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አማካይነት ተልኮ መፋፈሉ ተገለፀ።

ከመዝሄ



ከዕርዳታ ኘሮግራሞች አፈፃፀም ክትትል መምሪያ የተገኘው መረጃ እንዳመለከተው ከዚህ ዕርዳታ ውስጥ 21 ሺህ 964 ኩንታል እህል ፣ 727 ኩንታል ዘይት ፣ 2ሺህ 843 ኩንታል ከ70 አልሚ ምግብ ፣ 1ሺህ 948 ኩንታል ጥራጥሬ ፣ 200 ኩንታል ዱቄት የተላከ ሲሆን በካርቶን በታሸጉ ምግቦች ረገድም 300 ካርቶን ማርማላታ ፣ 50 ካርቶን ሰርዲን ፣ 139 ካርቶን ወተትና መጠናቸው የተለያዩ 16 ጣሳ በተለያዩ ክልሎች በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች እንዲደርስ ተደርጓል።

ምግብ ነክ ባልሆኑ ቁሳቁሶች ረገድም 50 ካርቶን ሣሙና ፣ 36 ሺህ 423 ኘላስቲክ ኩባያ ፣ 36ሺህ 423 ኘላስቲክ ሣህን ፣ 6ሺህ 384 ጀሪካን ፣ 2ሺህ 20 ጭልፋ ፣ 5ሺህ 41 ብረትድስት ፣ 1ሺህ 318 የሻይ ጀበና ፣ 606 ጆግ ፣ 666 ጥቅል ኘላስቲክ ሺት፣ 383 ድንኳን ፣ 13ሺህ 591

ኩንታል እህል ፣ 236 ኩንታል ዘይት ፣ 874 ኩንታል አልሚ ምግብ ፣ 783 ኩንታል ጥራጥሬ ፣ የተላከ ሲሆን ምግብ ነክ ባልሆኑ ቁሳቁሶች በኩልም 7ሺህ 432 ኘላስቲክ ኩባያ ፣ 7ሺህ 432 ኘላስቲክ ሣህን ፣ 1ሺህ 578 ጀሪካን ፣ 918 ብረት ድስት ፣ 918 የሻይ ጀበና ፣ 125 ጥቅል ኘላስቲክ ሽት፣ 6ሺህ 79ብርድልብስ ቁጥራቸው ከ24 ሺህ 534 እስከ 35ሺህ 928 ለሚደርሱ የክልሉ የጎርፍ ተጠቂዎች ተልኳል።

ለድሬዳዋ መስተዳደር የጎርፍ ሰለባዎች ደግሞ ፣ 2ሺህ ኩንታል እህል፣ 105 ኩንታል ዘይት፣ 404 ኩንታል አልሚ ምግብ ፣ 150 ኩንታል ጥራጥሬ እንዲሁም 300 ካርቶን ማርማላታ፣ 50 ካርቶን ሰርዲን ፣ 139 ካርቶን ወተትና 16 ጣሣ ወተት ለ10ሺህ ተረጂዎች እንዲደርሳቸው ተደርጓል። ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በተመለከተም 50 ካርቶን ሳሙና፣ 10 ሺህ ኘላስቲክ ኩባያ፣

10 ሸህ ኘላስቲክ ሣህን ፣ 2ሺህ ጀሪካን ፣ 2ሺህ ጭልፋ ፣ 2ሺህ 10 ብረት ድስት 150 የሻይ ጀበና ፣ 25 ጥቅል ኘላስቲክ ሸት ፣ 255 ድንኳን ፣ 4ሺህ ብርድልብስ ፣ 1ሺህ 150 ፍራሽ ተልኳል።

ከዚህም ሌላ በኦሮሚያ ክልል ለሚገኙ 19ሺህ 203 የጎርፍ ሰለባዎች 887 ኩንታል እህል፣ 28 ኩንታል ዘይት ፣ 277 ኩንታል አልሚ ምግብ ፣ 58 ኩንታል ጥራጥሬ የተላከ ሲሆን ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን በተመለከተም 7ሺህ 390 ኘላስቲክ ኩባያና፣ 7ሺህ 390 ኘላስቲክ ሣህን ፣ 800 ጀሪካን ፣ 363 ብረት ድስት ፣ 38 ጥቅል ኘላስቲክ ሸት ፣ 130 ድንኳን ፣ 1ሺህ 800 ብርድልብስ ፣304 ሺህ የጎርፍ መከላያ ዳይክ ለመስራት የሚያስችል ጆንያ እንዲደርስ ተደርጓል።

እንዲሁም በደቡብ ክልል 18 ሺህ 627 ለሚሆኑ የጎርፍ ተጠቂዎች 3ሺህ 40 ኩንታል እህል፣ 108 ኩንታል ዘይት፣ 441 ኩንታል አልሚ ምግብ ፣ 276 ኩንታል ጥራጥሬ ተልኳል። ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን በተመለከተም 2ሺህ 500 ኘላስቲክ ሣህን ፣ 250 ጀሪካን ፣ 20 ጭልፋ ፣ 1ሺህ 750 ብረት ድስት፣ 250 የሻይ ጀበና ፣ 250 ጆግ፣ 30 ጥቅል ኘላስቲክ ሸት ፣ 5 ድንኳን ፣ 1ሺህ ብርድልብስ የተላከ ሲሆን አንድ መቶ ሺህ ጆንያ ለጎርፍ መከላከያ ዳይክ መስሪያ እንዲደርሳቸው ተደርጓል።

እንዲሁም በአፋር ፣ በጋምቤላ ፣ በትግራይና በሶማሌ ክልል ለሚገኙ የጎርፍ አደጋ ሰላባዎች 81 ኩንታል እህል ፣ 73 ኩንታል ዘይት ፣ 865 ኩንታል አልሚ ምግብ ፣ 681 ኩንታል ጥራጥ ፣ እንዲደርሳቸው ሲደረግ ፣ ምግብ ነክ ባልሆኑ ቁሳቁሶች ረገድም ለእነዚሁ ክልሎች 35 ጥቅል ኘላስቲክ ሸት ፣ 278 ብርድልብስ ለትግራይ ብቻ ተልኳል።

በሌላም በኩል ለጋምቤላ ክልል የጎርፍ ተጎጂዎች ለህዳር ወር የሚሆን 4 ሺህ 637 ኩንታል የምግብ እህል ፣ 487 ኩንታል ብስኩት እና 139 ኩንታል ዘይት የተመደበ መሆኑን ከኤጀንሲው የዕርደታ ኘሮግራሞች አፈፃፀምና ክትትል መምሪያ ያገኘው መረጃ ያመለክታል።



## ለጥቅምት ወር ከ 176 ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል።

በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በምግብ ዕጥረት ሳቢያ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው መደበኛ ተረጂዎች እና በጎርፍና የውሀ መጥለቅለቅ አደጋ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች ለጥቅምት ወር በጠ ቅላላው 176 ሺህ 124.9 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል።

ከአመዝኤ የዕርዳታ ኘሮግራሞች አፈጻጸም ክትትል መምሪያ የተገኘው መርጃ እንደሚያመለክተው ለወሩ ከተመደበው ጠ ቅላላ ዕርዳታ ውስጥ 173 ሺህ 850 ኩንታል በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ቀሪው 2 ሺህ 574.9 ኩንታል ደግሞ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተመደበ ነው። በሌላም በኩል ለጥቅምት ወር ከተመደበው ጠቅላላ 176 ሺህ 124.9 ኩንታል ውስጥ 141 ሺህ 205.9 ኩንታል ለመደበኛ ተረጂዎች ቀሪው 34 ሺህ 919 ኩንታል ለጎርፍ ተጎጂዎች የተመደበ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

የዕርዳታ አመዳደቡም በየክልሉ እንደሚገኘው ችግር ስፋትና ጥልቀት የሚለያይ ሆኖ በዚሁ መሠረት ለመደበኛ ተረጂዎች ከተመደበው 141 ሺህ 205.9 ኩንታል ውስጥ ለሱማሌ 93 ሺህ 8 ኩንታል ፣ ለኦሮሚያ 34 ሺህ 218.9 ኩንታል ፣ ለአማራ 13 ሺህ 913 ኩንታል እና ለደቡብ ሕዝቦች 66 ኩንታል ተመድቧል።

በተመሳሳይም ለጎርፍ ተጎጂ ወገኖች

በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በምግብ ዕጥረት ሳቢያ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው መደበኛ ተረጂዎች እና በጎርፍና የውሀ መጥለቅለቅ አደጋ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች ለጥቅምት ወር በጠቅላላው 176 ሺህ 124.9 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል።

ከተመደበው ጠቅላላ 34 ሺህ 919 ኩንታል ውስጥ ለሱማሌ 25 ሺህ 083 ኩንታል ፣ ለጋምቤላ 5 ሺህ 263 ኩንታል ፣ ለአማራ 3 ሺህ 378 ኩንታል እና ለድ ዳዋ 1 ሺህ 195 ኩንታል የተመደበ መሆኑ ታውቋል።

## የብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ የዕርዳታ አሰባሰብ መርሀ ግብር አፀደቀ ለጎርፍ ተጎጂ ወገኖች ሁሉም የበኩሉን ድጋፍ እንዲያበርክት ጥሪ አቀረበ

በክረምቱ ወቅት በደረሰው ከፍተኛ የጎርፍ አደጋ ሳቢያ ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች መልሶ ለማቋቋም በሚደረገው ጥረት የብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሰብ ኮሚቴ 29.5 ሚሊዮን ብር ዕርዳታ ለማሰባሰብ የሚያስችሉ የተለያዩ ዝግጅቶችን ያካተተ የዕርዳታ ማሰባሰቢያ ዝርዝር ዕቅድ መርሀ ግብር አጸደቀ ። ለመርሀ ግብሩ ስኬታማነት ሁሉም ወገን የየበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲያበረክት ጥሪ ቀረበ።

ከመንግሥት መ/ቤቶች ፣ ከሃይማኖት ተቋማት ፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ፣ ከስቪክና ሙያ ማህበራት ተወካዮችንና ታዋቂ ግለሰቦችን በማካተት ያቋቋማቸው የልዩ ልዩ ገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ስድስት ኮሚቴዎች ያዘጋጁት ዝርዝር መርሀ ግብር በአፋጣቃ ወደ ተግባር ተሸጋግሮ ውጤታማ እንዲሆንም እንደተለመደው የኢትዮጵያን ሕዝብና ወዳጆች ተሳትፎና አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርቧል።

በክረምቱ ወቅት በደረሰው ከፍተኛ የጎርፍ አደጋ ሳቢያ ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች መልሶ ለማቋቋም በሚደረገው ጥረት የብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሰብ ኮሚቴ 29.5 ሚሊዮን ብር ዕርዳታ ለማሰባሰብ የሚያስችሉ የተለያዩ ዝግጅቶችን ያካተተ የዕርዳታ ማሰባሰቢያ ዝርዝር ዕቅድ መርሀ ግብር አጸደቀ ።



በዛ ው ዕለት ብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው ጥቅምት 6 ቀን 1999 ዓ.ም ባካሄደው 3ኛው መደበኛ ስብሰባ ላይ እንዳስታወቀው የጎርፍ ተጎጂዎችን ለዘለቄታው መልሶ ለማቋቋም መንግሥት እያደረገ ካለው ከፍተኛ ርብርቦሽ ጎን መላው የኢትዮጵያ ሕዝቦችና ወዳጆች በራሳቸው ተነሳሽነት በመስጠት ላይ ያሉትን የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ይበልጥ በማቀናጀትና በማስተባበር ለታለመው ዓላማ እንዲውል የተነደፉ የዕርዳታ ማሰባሰብ ስልቶችን መርምሮ ወደ ተግባር እንዲሸጋገሩ ወስኗል።

ብሔራዊ የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው የጎርፍ ተጎጂ ወገኖችን መልሶ ለማቋቋም የሚካሄደውን ድጋፍ ለማጎልበት ብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው በተለያዩ ዝግጅቶች ለማሰባሰብ የታሰበውንና በቴሌቶንና የምሳ ዝግጅት ኮሚቴ ፣ በስፖርት ፣ የሙዚቃና የቲያትር ኮሚቴ ፣ በሎተሪ ዝግጅት ኮሚቴ ፣ በሃይማኖት ተቋማት ኮሚቴ ፣ በውጪ ዕርዳታ አሰባሳቢ ፣ በኢንፎርሜሽን ሥርጭትና ኘሮሞሽን ኮሚቴዎች ተዘጋጅቶ በዓብይ ኮሚቴው የቀረበውን ዝርዝር የሥራ መርሀ ግብር ፣ ለማሰባሰብ ያቀዱትን የገንዘብ መጠንና ዝግጅቶቹን ለማካሄድ በሚያስፈልገው የወጪ ፍላጎት ዙሪያ ተወያይቷል።

በዕርዳታ አሰባሰቡ ዝርዝር መርሀ ግብር ዙሪያ በተደረገው ውይይት ወቅት በጎርፍ ለተጎዱ ወገኖች ለአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ዕርዳታና ለመልሶ ማቋቋም ቀደም ሲል 237.1

ሚሊዮን ያህል ብር ይፋ ዕርዳታ ጥያቄ መቅረቡን አስታውሰው ይህ መጠን ጎርፉ በህብትና በንብረት ላይ ያደረሰውን የጥፋት መጠን በተሟላ መልኩ አለማካተቱንና በአሁኑ ጊዜ ፍላጎቱ በተሻለና በጥናት በተደገፈ ሁኔታ እየተከለሰ መሆኑን ግንዛቤ ተወስዷል።

በመሆኑም ይህንን የዕርዳታና የመልሶ ማቋቋም ፍላጎት ለማሟላት በፌዴራል መንግሥት ደረጃ እየተካሄደ ካለው የዕርዳታ አሰባሰብ እንቅስቃሴ ጎን በየክልሎቹም በተመሳሳይ አደረጃጀት በጎርፍ የተጎዱ ወገኖችን የመደገፍ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የብሔራዊ የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴው አሳስቧል።

ኮሚቴው አያይዞም የጎርፍ አደጋው ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ መላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ተጎጂ ወገኖችን ለመደገፍ ላሳዩት ርብርቦሽ እንዲሁም የመንግሥት፣ የግልና ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን የችግሩን ትክክለኛ ገጽታ በሀገር ውስጥና በመላው ዓለም በማሳወቅ ረገድ ለተጫወቱት ሚና ያለውን አድናቆት ገልጸ ለቀጣይም ዕርዳታ ለማሰባሰብ ለተለያዩ ዝግጅቶች መሳካት መሰል ተግባራት እንደሚጠበቅ አሳስቧል።

## ከ29 ሚሊዮን በላይ ዕርዳታ ለማሰባሰብ መታቀዱ ተገለፀ

በአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች በ1998 ዓ.ም የክረምት ወራት በተከሰተው የጎርፍ አደጋ ሳቢያ የተጎዱ ወገኖቻችንን መልሶ ለማቋቋም ከሚያስፈልገው 237.1 ሚሊዮን ብር ውስጥ ወገን ለወገን ደራሽ ነው በጎርፍ ለተጎዱ ወገኖቻችንን እንርዳ በሚል መንፈስ ዕርዳታ ለማሰባሰብ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው ብሔራዊ የዕርዳታ አሰባሳቢ አብይ ኮሚቴ ከብር 29 ሚሊዮን ብር በላይ ዕርዳታ ለማሰባሰብ መታቀዱ ተገለፀ።

ይህ የተገለፀው በአብይ ኮሚቴውና በአብይ ኮሚቴው ሥር የተዋቀሩ የንዑሣን ኮሚቴዎች አባላት በተከሡተው የጎርፍ አደጋ ምክንያት የተጎዱ ወገኖቻችን መልሶ ማቋቋም ይቻል ዘንድ በመደረግ ላይ ስላለው የዕርዳታ ማሰባሰብ እንቅስቃሴ አስመልክቶ ጥቅምት 8 ቀን 1999 ዓ.ም በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የጋራ መግለጫ በሰጠብት ወቅት ነው።

አቶ ገብረመድህን በላይ የብሔራዊ ዕርዳታ አሰባሳቢ አብይ ኮሚቴ ሰብሳቢና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ም/ዋና ዳይሬክተር በዚሁ ጊዜ እንደተናገሩት ለጎርፍ አደጋ በሚጋለጡ አካባቢዎች ከ524 ሺህ በላይ ሕዝቦች እንደሚኖሩ መገመቱን አስታውሰው ፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በተደረገው ፈጣን ግምገማ በጎርፍ አደጋ የተጠቁና ከአካባቢያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች ከ200 ሺህ በላይ እንደሆነ በመረጃ በመረጋገጡ በእነዚህ ወገኖች ድጋፍ የሚውል ከ237.1 ሚሊዮን ብር ያህል ዕርዳታ ነሐሴ 19 ቀን 1998 ዓ.ም በአመዝኤና በሰብዓዊ ዕርዳታ ሰጭ አጋር ድርጅቶች መቅረቡን አመልከተዋል። ይህንኑ የዕርዳታ ፍላጎት ለማሟላት ዕርዳታው በዋናነት እየተጠበቀ ያለው ከኢትዮጵያውያንና በትውልድ ኢትዮጵያዊ ከሆኑ ወገኖች ነው ያሉት ም/ዋና ዳይሬክተሩ ዕርዳታ በማሰባሰብ ዙሪያ መንግሥት ግምባር ቀደም ሚናውን ለመወጣት ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የተወከሉ አባላት ያሉበት ብሔራዊ የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ አቋቁሞ በእስካሁኑ እንቅስቃሴ እስከ ጥቅምት 7 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ በጥ ገንዘብ 31 ነጥብ 89 ሚሉዮን ብር ያህል ከተለያዩ አካላት መለገሱን አስታውቀዋል። በዚህ የዕርዳታ ማሰባሰብ እንቅስቃሴ የተሳተፉ ኢትዮጵያዊያንና ሌሎች ወገኖችን ያመሰገኑት አቶ ገብረመድህን አመስግነው በአጠቃላይ ሕዝቡና ሌሎች

ለጋሽ አካላት በአብይ ኮሚቴው ሥር የተዋቀሩ ንዑሳን ኮሚቴዎች በሚያዘጋጁአቸው የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞች በመሳተፍ የወገን አለቃታነታቸውን እንዲያረጋግጡ በጎርፍ አደጋ ተጎጂ ወገኖችና በብሔራዊ ዐቢይ ኮሚቴው ስም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

እምነት ልዩነት ሳይገድቡን ለወገኖቻችንን ዕርዳታ ለማሰባሰብ መረባረብ አለብን ያሉት አቶ ውብሸት እሳቸው በሚመሩት የቴሌቶንና የምሳ ዝግጅት ኮሚቴ በኩል ሰፊ ዝግጅት በመደረግ ላይ በመሆኑ በውጭም ሆነ በአገር ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ በንቃት እንዲሳተፍ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች በ1998 ዓ.ም የክረምት ወራት በተከሰተው የጎርፍ አደጋ ሳቢያ የተጎዱ ወገኖቻችንን መልሶ ለማቋቋም ከሚያስፈልገው 237.1 ሚሊዮን ብር ውስጥ ወገን ለወገን ደራሽ ነው በጎርፍ ለተጎዱ ወገኖቻችንን እንርዳ በሚል መንፈስ ዕርዳታ ለማሰባሰብ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው ብሔራዊ የዕርዳታ አሰባሳቢ አብይ ኮሚቴ ከብር 29 ሚሊዮን ብር በላይ ዕርዳታ ለማሰባሰብ መታቀዱ ተገለፀ፡፡



ዐቢይ ኮሚቴው ሥር የተዋቀሩት የቴሌቶንና የምሣ ዝግጅት፣ የስጠርት ፣ ሙዚቃ፣ የቲያትርና ፊልምና ሥዕል ፣ የሉተሪ ዝግጅት ፣ የህይማኖት ተቋማት ፣ የውጭ ሀገር ዕርዳታ አሰባሳቢና የኢንፎርሜሽን ስርጭትና ኘሮሞሽን ንዑሣን ኮሚቴዎችም በየበኩላቸው ስላደረጉት ዝግጅትና ከህብረተሰቡ ስለሚጠበቀው ትብብር ማብራሪያ ሰጥተዋል ፣ አቶ ውብሸት ወርቃለማሁ የቴሌቶንና የምሣ ዝግጅት ኮሚቴ ሰብሳቢ በዚሁ “ወገን ለወገን ደራሽ ነው በጎርፍ አደጋ የተጎዱ ወገኖቻችንን እንርዳ” በሚል መርህ በተዋቀረው የዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ ስር ገብተው ለመሥራት ያነሳሳቸው ጎርፉ በድ ዳዋ ከተማ በተከሠተበት ወቅት በቦታው ተገቃተው የአደጋውን አስከፊነት በመመልከታቸው እንደሆነ ገልጸው፣ አዛኙና ሩህሩሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘወትር እንደሚያደርገው ሁሉ ዕርዳታውን በመለገስ የወገኖቹን እንባ እንደሚያብስ እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡ የጠለቲካና የሌላም የሌሉች ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎችም በየበኩላቸው ስላደረጉት ዝግጅት ሰፊ ማብራሪያ ያቀረቡ ሲሆን የውጭ ሀገር ዕርዳታ አሰባሳቢ ኮሚቴ 5 ዶላር ዋጋ ያለው ካሽ ኩፖን በማዘጋጀትና ይህንኑ ኩፖን በውጭ በሚገኙ ኢምባሲዎችና ሚሲዮኖቻችን በኩል በመሸጥ በዋናነት ከኢትዮጵያውያንና ከትውልደ - ኢትዮጵያውን ዕርዳታ ለማሰባሰብ ማቀዱን አስታውቋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የስፖርት ፣ የሙዚቃ ፣ የፊልምና የትያትር ኮሚቴ በስፖርቱ ዘርፍ የእግር ኳስ ፣ የሩጫ ውድድሮችን በማዘጋጀት በባህል ዘርፍ ከትያትርና ሲኒማ ቤቶች ጋር በመተባበር የሙዚቃ ፣ የፊልም ትርዒቶችን በማሳየትና ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ዕርዳታውን ለማሰባሰብ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ገልጿል፡፡ የሎተሪ ዝግጅት ኮሚቴም ባለ 3 ብር ልዩ ቶምቦላ በማዘጋጀት የሚያገኘው ገቢ ለወገኖቻችን መርጃ ለማዋል በዝግጅት ላይ መሆኑን አስታውቋል፡፡

# የስጠርት የሙዚቃ እና የትያትር ዝግጅት ኮሚቴ የዕርዳታ ማሰባሰብ ፕሮግራሙን ይፋ አደረገ

በጎርፍ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ በዕርዳታ አሰባሳቢ አብይ ኮሚቴ ሥር የተዋቀረው የሙዚቃ ፣ የቴያትር ፣ የስጠርት ፣ የፊልምና የሥዕል ኮሚቴ ሊሠራቸው ያቀዳቸውን ተግባራት ጥቅምት 10 ቀን 1999 ዓ.ም ለአባላቱ ይፋ አደረገ።

በጎርፍ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ በዕርዳታ አሰባሳቢ አብይ ኮሚቴ ሥር የተዋቀረው የሙዚቃ ፣ የቴያትር ፣ የስጠርት ፣ የፊልምና የሥዕል ኮሚቴ ሊሠራቸው ያቀዳቸውን ተግባራት ጥቅምት 10 ቀን 1999 ዓ.ም ለአባላቱ ይፋ አደረገ። በኮሚቴው ሥር ለዕርዳታ አሰባሳቡ እንቅስቃሴ የተዋቀሩት ንዑሳን ኮሚቴዎችም ህብረተሰቡ በልዩ ልዩ ዝግጅቶች በመታደም ተጎጂ ወገኖቹን እንዲደግፍ በሙያቸው የበኩላቸውን ድርሻ እንደሚወጡ አስታወቁ።

ኮሚቴው በተጠቀሱት ዝግጅቶች የካበተ ልምድና ሙያ ካላቸው የንዑሳን ኮሚቴ አባላት ጋር ስለ ፕሮግራሙ በሰጠው አጠቃላይ ይዘት ማብራሪያ እንዳስታወቀው በስጠርት ዘርፍ የእግር ኳስ ፣ የአትሌቲክስና የማርሻል አርት ዝግጅቶች ከጥቅምት እስከ ታህሳስ ወራት ባሉት ጊዚያት ይካሄዳሉ። የኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ዮሴፍ ዳኤሞ በዚሁ ጊዜ እንደገለጹት በእግር ኳስ ዝግጅት ረገድ በ8 ክለቦች መካከል የሚደረግ ውድድር የሚካሄድ ሲሆን ማንቼስተር ከቼልሲ ፣ ቸልሲ ከአርሲናል ጋር የሚያደርጓቸውን ውድድሮች በእስክሪን በማሳየት ገቢ ለማሰባሰብ ፕሮግራም ተይዟል።

በማርሻል አርት ስጠርት በኩልም ውሹ ፣ ካራቴ ፣ ወርልድ ቴኳንዶ ፣ እንተርናሽናል ቴኳንዶ ትርኢቶችና የከፍተኛ ክብደት ማንሳት ውደደሮችን በማካሄድ የሚገኘው ገቢ በጎርፍ የተጎዱ ወገኖችን መልሶ ለማቋቋም ለሚደረገው ጥረት እንደሚውል ያብራሩት የኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ዮሴፍ ዳኤሞ ሕብረተሰቡን በ 6 ኪሎ ሜትር የጎዳና ሩጫ እንዲሳተፍ በማድረግ ገቢ በማሰባሰብ ተጎጂ ወገኖችን ለመታደግ መታቀዱንም አስታውቀዋል።

በሙዚቃ ትያትርና ፊልም ዝግጅት ረገድም በመስቀል አደባባይ የሙዚቃ ፌስትቫል እና የፊልም ማሳየት ፌስቲቫል በማካሄድ ገቢ ለማሰባሰብ ከመታሰቡም በላይ የትያትርና የሲኒማ ቤቶች የተለያዩ ፊልሞች በማቅረብ ሕብረተሰቡ እየተዝናና ወገኑን የሚረዳበት ፕሮግራም መያዙን የገለጹት አቶ ዮሴፍ በትያትር ቤቶች ውስጥ ያሉትን ቲያትሮች ለህዝብ በማቅረብ በአንድ በኩል ዕርዳታ ለማሰባሰብ ዝግጅቱ መጠናቀቁን አስታውቀዋል። ለኮሚቴውና ለንዑሳን ኮሚቴው አባላት የአመዝኤ ም/ዋና ዳይ ክተርና የዕርዳታ አሰባሳቢ ዓቢይ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ገብረመድህን በላይ የጎርፍ ተጎጂ ወገኖችን ለመደገፍ ሕዝብ መንግሥትና ተባባሪዎች በእስከአሁኑ እያደረጉ ስላለው ጥረትና በአሁኑ ወቅት በተቀናጀ መልኩ ዕርዳታ ለማሰባሰብ ስለታለመበት ማብራሪያ ሰጥተዋል።